<u>**ከኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር ከግንቦት 7 ጋር መለያየቱን አስመልክቶ የተሰጠ መግለጫ**</u>

September 24, 2018



የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር 1993 ዓም አራት በትጥቅ ትግል ዘረኛውንና አፋኙን የወያኔ ስርዓት ሲፋለሙ የነበሩ ድርጅቶች ውህደት ፈጥረው ፣ መታገያ አቋማቸውንም ወያኔ ራሱ ያረቀቀውና ያጸደቀውን ህገ_መንግስት፣ ይህንን ተከትለው ለስልጣን እድሜ ማራዘሚያ የወጡ አዋጆችና ድንጋጌዎች በመቃወምና ስርዓቱም የተጠቀሱትን ለአገርና ህዝብ የማይጠቅሙ ድንጋጌዎች በሰላማዊ መንገድ ሊያስተካክል እንደማይችል በተረዱ፣ ለኢትዮጵያም የሚያስፈልጋት አምባ ገነን ስርዓትን በመሳሪያ አስወግዶ በመሳሪያ የሚገዛ ስርዓት መተካት ሳይሆን በሰላማዊ መንገድ ዲሞክራሲያዊ የስልጣን ሽግግር እንዲኖር አስፈላጊውን መስዋዕትነት መክፈል አለብን ብለው በተነሱ ዜጎች የተመሰረተ ድርጅት ነው። ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግና የወያኔውን ስርዓት ተግባር የማንደግም መሆናችንን ለታጋዩም ሆነ ለምንታገልለት ህዝብ መተማመኛ ይሆን ዘንድ የአባት አያቶቻችን የአርበኝነት አርማ አንስተን ለሃገራችንና ህዝባችን ስንል ሻማ ሆነን የአንድነትና ዲሞክራሲ ብርሃን እንሆናለን በሚል ጉዞውን አንድ ብሎ ጀመረ።

የአባቶቹንና አያቶቹን የአርበኝነት አርማ አንግቦ የተነሳው የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር ወገኑን መሰረት አድርጎ ስንቅና ትጥቅን ጨምሮ የወታደራዊ ስልጠና ቦታን ከኤርትራ መንግስት ድጋፍ ያገኝ ስለነበር ወደ አገር ውስጥ ገብቶ የተለያዩ ወታደራዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎችን በማድረግ ከጊዜ ወደ ጊዜ አመርቂ ውጤቶችን እያስመዘገበና ድርጅታዊ ቁመናውም እየጎለበተ ሲሄድ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር ከሚኖሩ ወገኖቹ በሚያገኘው ድጋፍ ታግዞ የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጅነቱን ያሳየና እውነተኛ የአንድነትና የዲሞክራሲ ሃይል መሆኑን ያስመሰከረ ድርጅት መሆኑ የሚታወቅ ነው። የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር ከሚያደርጋቸው ወታደራዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች ጎን ለጎን የአንድነትና ዲሞክራሲ ሃይል እንደመሆኑ ብሄርን መሰረት አድርገው ለዲሞክራሲ መስፈንና ለነጻነት የሚታገሉ ትጥቅ አንግበው የሚታገሉ ድርጅቶች ጋር ጥምረትና ግንባር በመፍጠር የተለያዩ ወታደራዊ እንቅስቃሴዎችን ማድረግ በቻ ሳይሆን በአንድነት

መስዋዕትነት እየከፈለ አመርቂ ውጤቶችን እያስመዘገበ የመጣ ድርጅት ነው። የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር ያደርጋቸው በነበሩት ተጋድሎዎች ያስመዘግባቸው የነበሩት ወታደራዊና ፖለቲካዊ ድሎች እንዲሁ የመጡ ሳይሆን እስከ ህይወት መስዋዕትነት ያሉትን ዋጋዎች እየከፈለና ድርጅታዊ አንድነትንም ለመጠበቅ ከዘረኛውና ከፋፋዩ ስርዓት የሚላኩ ሰርጎ ገቦችን ከመከላከል ባለፈም አላማውን አስረድቶ እየሸኘ ምሳሌ የሆነ ኢትዮጵያዊ ድርጅት ቢሆንም ጎን ለጎን ከውስጥም ሆነ ከአገር ውጭ ባሉ ድርጆትችና ቡድኖች ይደርስበት የነበሩ ፈተናዎች ሲመከት የቆየ መሆኑ ስለ ድርጅቱ የሚያውቅ ኢትዮጵያዊ የሚመሰክረው የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው። ይህን ሁሉ መስዋዕትነት እየከፈለ መራሩን ጉዞ የቀጻለው ድርጅታችን ኢትዮጲያን የተናጠል ትግል እየጎዳት ነው ብቻ ሳይሆን የአምባገነኑን የወያኔ ስርዓት እድሜ መራዘም ምክንያትም እየሆን ነው፣ህዝቡም ተባበሩ ወይ ተሰባበሩ የሚለው ምሬት ያዘለ ጥሪ ምላሽ መስጠት አለብን በሚል ተወያይቶ ለተግባራዊነቱም እንቅስቃሴ እያደረግን ባለበት ወቅት ለረጅም ጊዜ የአብረን እንስራ ውይይት ብናደርግም መስማማት ያልቻልነው ግንቦት 7 ከኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር ጋር አብሬ መስራት እፈልጋለሁ የሚል ጥያቄ ሲያቀርብ ለረጅም ጊዜ ሳንስማማ የቆየን ቢሆንም እስካሁን ያላስማሙን ነገሮች በመቅረፍ ረገድ እኛም የተወሰነ ርቀት እንሂድና ጥያቄውን ተቀብለን አብረን እንታገል በሚል የተጀመረው ውይይት ግንባር ሳይፈጠር ፣ በጥምረት የድርጅቶችን አካሄድ ወደ አንድ እናምጣ ሳይባል በቀጥታ ወቅቱ የሚጠይቀው አንድ ሆኖ በውህደት መታገል እንጅ የተናጠል ሂደቱ አያዋጣም በሚል ስምምነት ላይ ተደረሰ ።

በዚህም መሰረት የአርበኝነት ትግሉ ምንም ጥያቄ የሌለውና የማይቀየር መሆኑን አስምሮበት የተለያዩ ውህደቱን ይጎዳሉ የተባሉ ነጥቦች ተነቅሰው የውህደት ስምምነቱ ሰነድ ሆነው የሁለቱ ድርጅቶች አመራሮች ተፈራርመውበት በጥር 2 / 2007 ዓም ውህደቱ ይፋ ሆነ። ከውህደቱ ማግስት ጀምሮ ግን የአሰራርና የአመራር ችግሮች መታየት ቢጀምሩም በጧቱ ግጭት ውስጥ መግባት የለብንም በንግግር እንፍታቸው እየተባለ ጊዜ ቢወሰድም እየባሰና ጭራሽ በስራ አስፈጻሚው ውሳኔ የተሰጠባቸው አጀንዳዎች ተግባራዊ እንዳይሆኑ ሲደረግ፣ ሰራዊቱም የሚያቀርባቸው ጥያቄዎች በወቅቱ ምላሽ ሳያገኙ ሲቀሩ ከሰራዊቱ ጋር በቅርብ የሚገናኘው አመራር ጥያቄ ምላሽ መስጠት ባለመቻሉ ወደ አለመስማማት ሂደት ተገባ ።

ይህንና መሰል ድርጅታዊ ተግባራትን ማከናወን ባለመቻሉና ይባስ ብሎም አመራሩንና ሰራዊቱን የመለያየት አይነት ክስተቶች መታየት በመጀመራቸው ሰባት የስራ አስፈጻሚ አባላት ከሊቀመንበሩከዶክተር ብርሃኑ ጋር አንሰራም የሚል አቋም በመያዝ ለማስተካከል ቢሞከርም ረጅም ርቀት ሳይሄድ በሽምግልና ሰበብ እንደገና ወደ ስራ ቢገባም መሻሻል ሳያሳይ ወደባሰ ንትርክና ጭቅጭቅ በማምራቱ ጎራ ለይቶ በኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር አመራር ላይ ጫና በማሳደር ልዩነቱ እንዲሰፋ ሆነ። ከላይ የተጠቀሱትንና በተለይም የድርጅቱ አካሄድ የፖለቲካ ፓርቲ አይነት አካሄድን የሚያመላክቱ ነገሮች መታየት በመጀመራቸውና ሰራዊቱም የአርበኝነት ትግሉ እጁ እየተጠመዘዘ ነው፣ እኛ ደግሞ ውርሳችን አርበኝነት ትርፋችን ታሪካዊነት ነው ብለን የተነሳን አርበኞች ግለሰብ ለማንገስ አን ታገልም በማለት ትግሉን ጥለው እንዲበተኑ ሲደረግ መጨረሻውን እናያለንና፣ የወንድሞቻችን ደም ረግጠን አንወጣም ያሉ ብቻ ሲቀሩ በተለያየ ጫና እንዲበተኑ ተደርጓል። ከዚህም በኋላ በጉባኤ ስም የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር አመራሮችን በማስወገድ ድርጅቱን የፓርቲ ቅርጽ ለማስያዝ በተደረጉ ሂደቶች ይህንንም ለማስፈጸም ተብሎ በተጠራው ጉባኤ ላይ የተሳተፉ አመራሮች በሙሉ ካሁን በኋላ በአመራርነት አንሰራም ብለው በአቋማቸው ሲወጡ ፣ የግንቦት 7 አመራሮች የሚፈልጉትን አይነት የፓርቲ መዋቅር ነድፈው ጉባኤያቸውን አካሂደዋል። የፖለቲካ ፓርቲ እንቅስቃሴው ሊያስተባብሉት በማይችል መልኩ ገና አለ የተባለው ሰራዊት አገሩ ሳይገባ በፖለቲካ ፓርቲነት ተመዝግበው ለስልጣን እንደሚወዳደሩ ማወጃቸው ከውህደቱ ጀምሮ ለነበረው አርበኛውን የማዋከብና ከሂደትለማድረጋቸው ማረጋገጫ ነው ብለን እናምናለን። በነዚህ ሂደቶች ውስጥ የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር አመራርና ታጋዮች እንዲታሰሩ ሌሎች ደግሞ አንገታቸውን ደፍተው እንዲቆዩ ቢደረግም፣ ወደፊት ማብራሪያ በምንሰጥባቸው ምክንያቶች ለ18 አመታት የታገልንለትና ወንድሞቻችን ህይወታቸውን የሰጡለት

የአርበኝነት ትግል ለስልጣን ጥመኞች መሸጋገሪያ አይሆንም፣በሚል በግንቦት 7 አመራሮች ምክንያት ድርጅቱን ጥለን ወጥተን በአገር ውስጥ የፋኖውን ትግል የተቀላቀልንም ሆነ በሌላ ድርጅት ተጠልለን የቆየን ታጋዮች የድርጅታችን ህልውና ማረጋገጥ አለብን ብለን ከግንቦት7 ጋር ለመለየት ውሳኔ ላይ ደርሰናል። ድርጅታችን የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር ወደፊት በሚኖረው የትግል ሂደት የሚታገልበትን አላማና የትግል መስመር በቅርቡ በሚያካሂደው ጉባኤ ላይ የሚወስን ይሆናል። የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባርን ትንሳኤ ለማረጋገጥ በምናደርገው እንቅስቃሴ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሃገር የምትኖሩ ከግንቦት 7 ጋር ያደረግነውን ውህደት በመቃወምና ከውህደቱም በኋላ በግንቦት 7 አመራሮች በደረሰባችሁ ጫና ከድርጅቱ የተገለላችሁ አባላትና ደጋፊዎቻችን አስፈላጊውን ሁሉ እገዛ ለማድረግ ከጎናችን እንድትቆሙ በትግሉ ሰማዕታት ስም ወገናዊ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን። የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር

መስከረም 13/2011 ዓም